መልእክት አምስት

## የተነቃቃ ኑሮ በመኖር እና በእረኝነት እንክብካቤ በመድከም ለጌታ መምጣት ራሳችንን ማዘጋጀት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 2 ቆሮ. 4፡16-18፤ ዮሐ. 21፡15-17

**I. ለጌታ መምጣት ራሳችንን ለማዘጋጀት የተነቃቃ ኑሮ፣ ዕለት ዕለት የመታደስ ኑሮ ያለው በመሆን (2 ቆሮ. 4፡16-18) ድላችንን መጠበቅ ያስፈልገናል፤ ይህ መታደስ በየማለዳው እንደገና መታደስ አለበት (ማቴ. 13፡43፤ ሉቃ. 1፡78-79፤ ምሳ. 4፡18፤ መሣ. 5፡31)፡-**

ሀ. የየለቱ አዲስ ጅማሬ እንዲኖረን ጌታን በማለዳ መደሰት አለብን—መዝ. 119-147-148።

ለ. እንድንታደስ በየማለዳው ፀሐያችን የሆነውን ጌታ ኢየሱስ በውስጣችን እንዲወጣ መፍቀድ አለብን—ሉቃ. 1፡78-79፤ ሚል. 4፡2፤ መሣ. 5፡31፡-

1. ከጌታ ጋር ኅብረት ለማድረግ በማለዳ መነሣት አለብን፣ እንዲህ ብለን መጸለይም እንችላለን "ስለ አዲስ ጅማሬ ጌታ ተመስገን፤ ይህ ቀን በሕይወቴ የማይረሳ ቀን ይሁንልኝ"፤ የየማለዳው መነቃቂያ የምንለው ይህንን ነው።
2. አዲስ ጅማሬ ይኖረን ዘንድ ክርስቶስ የኃጢአት መሥዋዕታችን በመሆኑ ላይ በመመሥረት በየማለዳው እርሱን እንደሚቃጠለው መሥዋዕታችን እና እንደ ሰላም መሥዋዕታችን ማቅረብ አለብን፤ ይህንን ማድረግ ያለብን በየዕለቱ ብቻ ሳይሆን በጣፋጭነትና በጥልቀትም ጭምር ማድረግ አለብን—ዘሌ. 6፡12-13።
3. በየማለዳው ክርስቶስን እንደሚቃጠለው መሥዋዕት መውሰድ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እርካታ እንደኖረው ማንነት እና እንዲህ ያለ ኑሮ መኖር እንደሚያስችለን ሕይወት እርሱን መውሰድ ነው—1፡9፤ 6፡12-13፤ ዮሐ. 5፡19፣ 30፤ 6፡38፡፤ 7፡18፤ 8፡29።

ሐ. የተነቃቃ ኑሮ እንዲኖረን፣ ጌታን ፈጽመን የምንወድ እና የክርስቶስ ሙሉ ድሰታ እና እርሱን የማትረፍ የየዕለት ግብ ይዘን ለእርሱ የምንኖር መሆን አለብን—1 ቆሮ. 2፡9፤ 2 ቆሮ. 5፡14-15፤ ፊልጵ. 3፡14።

መ. የመሠዊያውን እና የድንኳኑን ኑሮ የምንኖር መሆን አለብን—ዘፍ. 12፡7-8፤ 13፡3-4፣ 18፡-

1. የእግዚአብሔር ለእኛ መገለጥ መሰጠታችንን ያመጣል፣ መሠዊያን እንድንሠራ ያደርገናል፤ መሠዊያ ለእግዚአብሔር ዓላማ የሆንነውን እና ያለንን ሁሉ ለእርሱ በማቅረብ እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው፤ መሠዊያውን መሥራት ማለት ሕይወታችን ለእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር ሕይወታችን ነው ማለት ነው፤ የሕይወታችን ትርጉም እግዚአብሔር ነው ማለት ነው—8፡20-21፤ ዘጸ. 29፡18-22።
2. የድንኳኑን ኑሮ መኖር፣ የሚበልጠውን አገር የምንናፍቅ እና በእግዚአብሔር የተገነባችውን ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን በጉጉት የምንጠባበቅ በምድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች እንደሆንን ማወጃችን ነው—ዕብ. 11፡9-10፣ 13፣ 16።

ሠ. በየዕለቱ የሚታደስ መነቃቃት ያለን መሆን በየዕለቱ ትኩስ የሆነ መለወጥ ያለን መሆን ነው፣ ሕይወታችንን በሙሉ በዚህ መለወጥ ውስጥ ከቶየን፣ እስከንበስል ድረስ በጌታ ሕይወት እናድጋለን—ሮሜ 12፡2፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ ዕብ. 6፡1።

ረ. በአራት ነገሮች በኩል ዕለት ዕለት እንታደሳለን፤ በመስቀሉ (2 ቆሮ. 4፡10-12፣ 16-18)፤ በመለኮታዊው ሕይወት በምንታደስበት፣ እንደገና በምንሠራበት እና በአዲስ ቅርጽ በምንሠራበት በመንፈስ ቅዱስ (ቲቶ 3፡5)፣ በተዋሐደው መንፈሳችን (ኤፌ. 4፡23) እና በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል (5፡26)።

ሰ. ወደ ጌታ ማዕድ በአዲስነት መምጣት አለብን (ማቴ. 26፡29)፤ ጌታ አሮጌ ማዕድ አይወስድም፤ "ይቅርታ፣ ይቅር በለኝ" ማለትን በመማር መታደስ ያስፈልገናል።

ሸ. በመከራ ውስጥ እያለን፣ የእርሱን ማደስ እንለማመድ ዘንድ በየማለዳው የጌታን አዳዲስ ርኅራኄዎች መቀበል ያስፈልገናል፤ አለበለዚያ፣ እንደዚያው እንቀራለን፣ ያለፍንበት መከራም ከንቱ ይሆናል—ሰቆ. 3፡22-24፤ 2 ቆሮ. 4፡16-18።

**II. ለጌታ መምጣት ራሳችንን ለማዘጋጀት፣ የክርስቶስን አካል የምታፈራው ቤተ ክርስቲያን የሆነውን የእግዚአብሔርን መንጋ ለመንከባከብ የእርሱን ጠቦቶች ለመመገብና የእርሱን በጎች በእረኝነት ለመንከባከብ በክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ውስጥ በመሳተፍ ድላችንን መጠበቅ አለብን—ዮሐ. 21፡15-17፤ 1 ጴጥ. 2፡25፤ 5፡1-4፤ ዕብ. 13፡20-21፡-**

ሀ. ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መከናወን በጌታ ኢየሱስ አገልግሎት ምሳሌ መሠረት ሰዎችን በእረኝነት መንከባከብ ያስፈልገናል—ማቴ. 9፡36፤ ዮሐ. 10፡11፤ ዕብ. 13፡20፤ 1 ጴጥ. 5፡4፡-

1. ለመካንነታችን ምክንያቱ የአብ አፍቃሪ እና ይቅር ባይ ልብ ስለሌለን እና የአዳኙ በእረኝነት የሚንከባከብ እና የሚፈልግ መንፈስ ስለሌለን ነው—ሉቃ. 15፡1-24።
2. ሰዎችን በኢየሱስ ስብዕና ማስደሰት (ደስታ እና ምቾት እንዲሰማቸው ማድረግ) አለብን (ማቴ. 9፡10፤ ሉቃ. 7፡34)፤ ሰዎችን በክርስቶስ መለኮትነት መመገብ (በአገልግሎቱ ሦስት ደረጃዎች ሁሉን-ባካተተው ክርስቶስ መመገብ) አለብን (ማቴ. 24፡45-47)።
3. ክርስቶስ አንዲት ስነ ምግባር የጎደላትን ሴት የሚጠጣው ውኃ እንድትሰጠው ጠይቆ በማስደሰት እንደ ሕይወት ውኃ ወንዝ በሚፈሰው በሦስታንዱ አምላክ እርሷን ለመመገብ፣ ሆን ብሎ በተለዋጭ መንገድ ወደ ሲካር ዞሮ በመሄድ በሰማርያ በኩል ለማለፍ ግድ ሆነበት—ዮሐ. 4፡3-14።
4. ኃጢአት እንደሌለበት ማንነት፣ አመንዝራይቱን ሴት አልኮነናትም፣ ነገር ግን በፍትሃዊ መልኩ ለኃጢአቶቿ ይቅርታ ለማግኘቷ እና በሕይወታዊ መልኩ ከኃጢአቶቿ ነፃ ለመውጣቷ አስደሰታት (8፡1-11፣ 32፣ 36) ክርስቶስ በመሰቀሉ በኩል መጀመሪያ የዳነው ሰው የሞት ፍርድ የተፈረደበት ወንበዴ መሆኑም ትርጉም ያለው ነው (ሉቃ. 23፡42-43)።
5. ጌታ ወደ ኢያሪኮ የሄደው አንድን ሰው፣ የቀራጮች አለቃን ለማግኘት ብቻ ነበር፣ ስብከቱም የእረኝነት እንክብካቤ ነበር (19፡1-10)፤ እጆቹንም በልጆቻቸው ላይ በመጫን ወላጆችን አስደሰተ (ማቴ. 19፡13-15)።
6. እንደ ወርቃማ መቅረዞች አብያተ ክርስቲያናትን በመንከባከቡ፣ የዐረገው ክርስቶስ "የሚመላለሰው ክርስቶስ" እና "የሚናገረው መንፈስ" ነው፤ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል በመመላለሱ፣ የእያንዳንዱን ቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ያውቃል፣ በሚያየውም ነገር መሠረት በአብያተ ክርስቲያናት ያሉ ቅዱሳንን ሁሉ ድል ነሺዎቹ ለማድረግ በሆነ ዓላማ በገንባ አፍራሽ ቅንባሮ እና በሕይወታዊ መልኩ ይለወጡ ዘንድ ይናገረናል—ራእ. 1፡12-13፤ 2፡1፣ 7።

ለ. የእግዚአብሔርን መንጋ ለመንከባከብ ቅዱሳንን እንደ ሞግዚት እናት እና እንደ መካሪ አባት በእረኝነት የተንከባከበውን የሐዋርያውን ጳውሎስ ምሳሌ በመከተል ሰዎችን በእረኝነት መንከባከብ ያስፈልገናል—1 ተሰ. 2፡7-8፣ 11-12፤ 1 ጢሞ. 1፡16፤ ሐዋ. 20፡28፦

1. ጳውሎስ በኤፌሶን ያሉትን ቅዱሳን "በጉባኤም በየቤታቸው" (ቁ. 20) በማስተማር እና ለሦስት ዓመታት እያንዳንዱን ቅዱሳን በእንባ በመገሠጽ (ቁ. 31፣ 19) የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ እየነገራቸው (ቁ. 27) በእረኝነት ተንከባከባቸው።
2. ጳውሎስ ለአማኞች የቅርብ ግድ መሰኘት ነበረው (2 ቆሮ. 7፡2-7፤ ፊልሞ. 7፣ 12)፣ ደካሞቹን ለማግኘት ወደ እነርሱ ደረጃ ዝቅ ብሎ ወረደ (2 ቆሮ. 11፡28-29፤ 1 ቆሮ. 9፡22፤ ተዛ. ማቴ. 12፡20)።
3. ጳውሎስ ስለ ቅዱሳን፣ ያለውን ሁሉ፣ ማለትም ገንዘቡን ለመከፈል፤ የሆነውን ሁሉ፣ ማለትም ራሱን ለመከፈል ፈቃደኛ ነበር (2 ቆሮ. 12፡15)፤ ሌሎች ክርስቶስን እንዲደሰቱት ራሱን የሚሠዋ፣ ወይንን ከሚያመርተው ክርስቶስ ጋር አንድ የሆነ የመጠጥ መሥዋዕት ነበር (ፊልጵ. 2፡17፤ መሣ. 9፡13፤ ኤፌ. 3፡2)።
4. ጳውሎስ መንፈስን በማገልገል ሰዎችን ማክበር ይችል ዘንድ እግዚአብሔርን ለማክበር በመንፈስ ተመላለሰ—2 ቆሮ. 3፡3፣ 6፣ 8፤ ገላ. 5፡16፣ 25፤ መሣ. 9፡9።
5. ጳውሎስ በትምህርቱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ለማሳደግ ቤት፣ እነርሱን ለመፈወስ እና ለመመለስ ሆስፒታል፣ እነርሱን ለማስተማር እና ለማነጽ ትምህርት ቤት እንደሆነች አመልክቷል—ኤፌ. 2፡19፤ 1 ተሰ. 5፡14፤ 1 ቆሮ. 14፡31።
6. ለክርስቶስ አካል መገንባት ምንም ለመሆናችን እና ምንም ለማድረጋችን እጅግ የላቀው መንገድ ፍቅር መሆኑን ጳውሎስ ገልጧል፤ ፍቅር ያሸንፋል—8፡1፤ 12፡31፤ 13፡4-8፤ ኤፌ. 1፡4፤ 3፡17፤ 4፡2፣ 15-16፤ 5፡2፤ ራእ. 2፡4-5፤ ቆላ. 1፡18፤ 1 ተሰ. 1፡3።

© 2023 Living Stream Ministry